# አንድነትና መኢአድ በመጪው ምርጫ ያላቸው ስፍራ

## ክፍል አንድ

ኢብሳ ነመራ

12-24-14

ባለፈው ዕሁድ ታህሳስ 12፣ 2007 ዓ/ም በመላው ኢትዮጵያ በግንቦት ወር የሚካሄደው 5ኛው ዙር ምርጫ ላይ የሚሳተፉ የህዝብ ታዛቢዎቸ ምርጫ በመላው ሃገሪቱ በሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ተካሂዷል። የተመረጡት የህዝብ የምርጫ ታዛቢች ቁጥር 250 ሺህ ገደማ ነው። የህዝብ ታዛቢዎቹ፤ ምርጫ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ የሚያውቃቸው፣ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆኑና በሚኖሩበት አካባቢ በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። እንዲሁም አንድም የምርጫ ጣቢያ ሳይተርፍ በታዛቢነት የሚሳተፉ በመሆናቸው ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ ከየትኛውም ታዛቢ በላይ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

ከመጪው ታህሳስ 16 ጀምሮ ደግሞ በምርጫው ላይ ለመሳተፍ የመወዳደሪያ ምልክት የወሰዱት ፓርቲዎች እጩዎቻቸውን ያስመዘግባሉ። ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ባለፈው ሳምንት ማገባደጃ ላይ በሰጠው መግለጫ ስልሳ ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎቸ በምርጫው ላይ ለመሳተፍ ምልክታቸውን አስገብተዋል። እነዚህ ፓርቲዎች በፌደራልና በክልል ደረጃ የሚወዳደሩ ናቸው።

ይሁን እንጂ በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚወዳደሩ ሁለት ፓርቲዎች፣ ማለትም የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ (አንድነት) የተሰኙ ፓርቲዎች ማሟላት የሚቀራቸው ነገረ መኖሩን ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አሳውቋል።

ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መኢአድና አንድነት ያለባቸውን የአመራር አለመግባባት ችግር ፈትተው በአንድ ሳምንት ውስጥ እንዲያሳውቁ አሳስቧል። የአመራር አለመግባባት ችግራቸውን ፈትተው ለቦረዱ ካላሳወቁ የመወዳደሪያ ምልክታቸውን ለማፅደቅ እንደሚቸገር ነው ቦረዱ ያሳወቀው። ፓርቲዎቹ የአንድ ሳምንት ግዜ የተሰጣቸው

በዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ተሳትፏቸውን እንዲወጡ ለማስቻል መሆኑን የቦርዱ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና አስታውቀዋል።

ይህን ተከትሉ ሃገሪቱ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት ከ60 በላይ ከሚሆኑ ፓርቲዎች መኢአድና አንድነት ላይ የተፈጠረው መጓተት ግር ያሰኛቸው ወገኖች ተደምጠዋል። ሁለቱ ፓርቲዎች በቅረቡ ገብተወበት የነበረውን አባሎቻቸውንና ደጋፊያቸውን ግራ ያጋባ የአመራር ውዝግብና ሹም ሽር የሚያውቁ ግን፣ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ "ፓርቲዎቹ በውስጣቸው ያለውን የአመራር አለመግባባት እንዲፈቱ" በሚል ያቀረበላቸው ጥያቄ ምንጭና ምንነት ላይ ግንዛቤ አላቸው።

በዚህ ዙሪያ ያለውን እውነታ ለመረዳት ከአንድ ወር ቀደም ብሎ በመኢአድና በአንድነት ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን ሁኔታ ማስታወስን ይሻል። መኢአድ ከወር በፊት ፓርቲውን ለሁለት ዓመት ገተደማ በሊቀመንበርነት ሲመሩ እነደነበረ ሲነገርላቸው የቆየውንና ህዝብም በሊቀመንበርነት የሚያውቃቸውን አቶ አበባው መሃሪ፣ ሰውየውም ሆኑ የፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ባልጠበቁት ድንገተኛ አኳኋን ከስልጣናቸው አስወግዷቸዋል። በአቶ አበባው ምትክ ከሁለት ዓመት በፊት ከፓርቲው ታግደው የነበሩት አቶ ማሙሸት አማረ ሊቀመንበረ ሆነው ተሹመዋል።

ፓርቲው የአመራር ለውጥ ማደረጉ በራሱ ምንም ልዩ ነገር የለውም። ይሁን እንጂ ይህ ሹም ሽር የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ አባላትና ሌሎች አባላት እነዲሁም ደጋፊዎች ግራ ያጋባ ውጥንቅጡ የወጣ ነው። በድንገት ከሃላፊነታቸው የተነሱት አቶ አበባው መሃሪ እና ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደፓረቲው ከፍተኛ ስልጣን የመጡት አቶ ማሙሸት አማረ በየወገናቸው የሚናገሩት ነገር የተለያየና አንዱ የሌላውን ህጋዊነት የሚያጣጥል ነው።

አቶ አበባው መሃሪ እንደሚናገሩት የፓርቲው የቀድሞ ሊቀመንበር ኢ/ር ሃይሉ ሻውል ከሃላፊነታቸው ቢሰናበቱም "የፓርቲው የበላይ ጠባቂ" የሚል ማእረግ ተሰጥቷቸው ተቀምጠዋል። ይህ የፓርቲ የበላይ ጠባቂ የተባለ ሃላፊነት በፓርቲው ህገደንብ ውስጥ የለም። የኢ/ር ሃይሉ ሻውል የበላይ ጠባቂ ተብሎ መሰየምን ግን አቶ አበባው መሃሪም ተስማምተውበታል። በቅርቡ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት ሲወስን ጠቅላላ ጉባኤውን

የመጥራት ስልጣን ያለው ሊቀመንበሩ፣ ማለትም አቶ አበባው መሃሪ ቢሆኑም በፓርቲው ህገደንብ ላይ ምንም ስልጣን የሌላቸው ኢ/ር ሃይሉ በጉዳዩ ውስጥ ገብተው ጠቅላላ ጉባኤ ጠሪ ሆነዋል። አቶ አበባው ይህ አካሄድ የፓርቲውን ህገደንብ የጣሰ መሆኑን ቢገነዘቡም "ዋናው ጠቅላላ ጉባኤው መጠራቱ ነው" በሚል በዝምታ ማለፋቸውን ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢ/ር ሃይሉ ሻውል ከሁለት ዓመታት በፊት እርሳቸው የፓርቲው ሊቀመንበር በነበሩበት ወቅት በተፈጠረ አለመግባባት ከፓርቲው የታገዱትን አቶ ማሙሸት አማረና ቡድናቸውን በመኖሪያ ቤታቸው ሰብስበው "እርቅ" የተሰኘ ስብሰባ ያካሂዳሉ። ከውጭ የመጡ የፓርቲው አባላትም የተሳተፉበት ይህ ስብሰባ ለፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስፈልግ ገንዘብ የማሰባሰብ አጀንዳንም የያዘ ነበረ። እነአቶ ማሙሸተ ድሮም የተጣሉት ከኢ/ር ሃይሉ ሻውል ጋር በመሆኑ እርቁ እርሳቸውን እንደማይመለከት መናገራቸውን የገለፁት አቶ አበባው፣ በመጨረሻ እርቁ ቢፈፀምም እርቁ ግን "ስምምነት ነበረው" ብለዋል። ይህም "ከእነማሙሸት አማረ ጋር ያሉትና በእርቁ ላይ የተሳተፉት አስራአራት ያህል ግለሰቦች፣ የጠፉ የፓርቲውን ንብረት ጉዳይ ቀረበው እንዲያስረዱ፣ እንዲሁም ከእነዚህ ከታረቁ ገለሰቦች ውጭ ሌላ ሰው ወደጠቅላላ ጉባኤ ይዘው እንዳይገቡ" የሚል ነበር።

በኢ/ር ሃይሉ ሻውል መኖሪያ ቤት ለሶስት ቀናት ያህል የተካሄደው የ"እርቅ" ስብሰባ እንዳበቃ ከፓርቲው ታግደው የነበሩትና ከሁለት ዓመት ወዲህ በተካሄዱ ጉባኤዎች ተሳትፈው የማያውቁት እነማሙሸት አማረ የተገኙበት ጠቅላላ ጉባኤ ተሰበሰበ። እነአቶ ማሙሸት በቅርቡ መኢአድ "ከአንድነት ጋር እዋሃዳለሁ" ብሎ የጠራው ጉባኤ ላይ ለመገኘት ቢመጡም በመከልከልከላቸው እስከድብድብ የዘለቀ አለመግባባት ተፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል። ይህ በሆነ በአንድ ወር ያህል ግዜ ውስጥ የተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ነው በድንገት የተገኙት። ያም ሆነ ይህ በኢ/ር ሃይሉ መኖሪያ ቤት አስራ አራቱ ሰዎች ብቻ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ እንዲገኙ ከእነአቶ አበባው ጋር ስምምነት ላይ ደርሰው የነበረ ቢሆንም፣ ተጨማሪ 1መቶ ሃምሳ ሰዎችምን ይዘው ወደጠቅላላ ጉባኤ እንደገቡ ነው አቶ አበባው የተናገሩት።

ይህን ጉባኤ መምራት የነበረባቸው አቶ አበባው ቢሆኑም ከፓርቲ ሊቀመንበርነታቸው ከተሰናበቱ ሁለት አመት ገደማ ያስቆጠሩት ኢ/ር ሃይሉ፣ አቶ አበባውን ከመድረክ ላይ ጎትተው አውርደው ስብሰባውን መርተዋል። ኢ/ር ሃይሉ ይህን ያደረጉበት ምክንያት "አቶ አበባው ከሁለት ዓመት በፊት የተመረጡበት ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ያልተሟላበት በመሆኑ የአቶ አበባው ሊቀመነበርነት ህጋዊ አይደለም" የሚል ነው። በዚህ አኳኋን አቶ አበባው ባልጠበቁት አኳኋን እነአቶ ማሙሸት ይዘዋቸው ወደጉባኤው በገቡ "ጥሪ ያልተደረገላቸው" 1መቶ ሃምሳ ሰዎች ተሳትፎ ጠቅላላ ጉባኤው አዲስ ሊቀመነበር እንዲመርጥ ተደረገ። አቶ አበባው በዚህ አኳኋን ሊቀመንበርነታቸውን በድንገት እጡ። በምትካቸው ከፓርቲው ተሰናብተው የነበሩት በኢ/ር ሃይሉ ሻውል መኖሪያ ቤት በተካሄደ እርቀ ጉባኤ ወደፓርቲው የተመለሱት አቶ ማሙሸት አማረ በድንገት የፓርቲው ሊቀመነበር ሆነው ተሰየሙ።

እዚህ ላይ ሁሉም የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በኢ/ር ሃይሉ ሻውል መሪነት የተከናወነውን ድንገተኛ የአመራር ለውጥ አልተቀበሉም። ከየአካባቢው የመጡ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በወቅቱ ቅሬታቸውን ገልፀው እነደነበረም ይታወሳል። በወቅቱ በመገናኛ ብዙሃን ቅሬታቸውን አቅረበው ከነበሩት መሃከል የተወሰኑትን ላስታውሳችሁ።

*አቶ በጋሻው ዳምጤ በሰሜን ሸዋ ቆጥ ወረዳ የመኢአድ ሰብሳቢ "የተጠራነው ለፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ነው። ከስብሰባው ውስጥ ግን በፊት ያለተነገረን አጀንዳ ቀረበ። እሱም ከእነማሙሸት አማራ ጋር እርቅ መደረጉን ተነገረን። የሚገርመው ማሙሸት አማራ በወረዳዎች ያዋቀረው መስመር መኢአድን ለመበታተን የተሰለፉ ናቸው። ምክንያቱም እሱ ያዋቀራቸው ቡድኖች በየወረዳው እየሄዱ በደጋም በቆላም ሽፍታ ተመድቧል እያሉ የመኢአድ አባላትን የሚያስፈራሩ ናቸው። እነዚህ ቡድኖች መታረቃቸው ችግር አይኖረው ይሆናል፣ ሆኖም ግን እርቅ ከሆነ ሌሎችም በ97 ዓ.ም ከፓርቲው የተገለሉ ሁሉም መጥተው እርቅ ቢፈጸም የሚል ጥያቄ ያቀረብን ቢሆንም ሰሚ አጣን።*

*ሌላው በፓርቲያችን መተዳደሪያ ደንብ አንድ ሰው ሶስት ወር ወርሃዊ ክፍያውን ካልከፈለ በምንም መልኩ አመራር ሆኖ ሊመረጥ አይችልም። አባል ሆኖም አይቀጥልም። ይህም ሆኖ እነዚህ ሰዎች በእርቅ የሚገቡ ከሆነ ከፖለቲካ አመራርነት ርቀው እንዲቀመጡ*

*ጉባኤው ጥያቄ አቀረበ። ይህ ጉዳይ ብዙ ውይይት እንዳይደረግ በስብሰባው መካከል የሚረብሹ በርካታ ሰዎች ገብተዋል። ከሁሉ የሚገርመው ጉባኤውን መቀላቀላቸው ሳይሆን ወደ ምርጫ እንዲገቡ ተደርጎ በተደራጀ ቡድን እንዲመረጡ ተደረገ። ከፍተኛ ረብሻም በስብሰባው መካከል ተነስቶ ነበር።*

*ሌላው፤ የተመራጭ ቆጠራ ሲደረግ በአይናችን የወጡት እጆች ትንሽ ሆነው እያየን ወደ መድረኩ ሲነገር እጅግ የተጋነነ ውጤት ሆኖ ሲነገር ነበር። በእውነት ለመናገር ከሰሜን የመጣነው ከልባችን አዝነን ነው ከጉባኤው የወጣነው። አንድ መሆናችን ባልከፋ በዚህ መልኩ ሁኔታዎች መከናወናቸው ግን አሳዛኝ ተግባር ነው። እኔ ከፕሮፌሰር አስራት ጀምሮ አደራጅ ነበርኩ። ለምርጫም ቀርቤ ተወዳድሪያለሁ። በዚህ ፓርቲ ውስጥ ማን ምን እንደሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን። በዚህ እድሜዬ ይህን ሕገወጥ ተግባር መመልከቴ ከልብ አዝናለሁ። በተለይ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ሁሉንም ነገር እያወቁ ይህን ማድረግ ለምን እንደፈለጉ ግልፅ አይደለም።”*

***ወ/ሮ ደስታ ካሳ ከደብረብርሃን ከቀይጥ ወረዳ፣ የባሶ አደራጅ እና በዞኑ የመኢአድ የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ*** *“እኛ በዚህ ፓርቲ ውስጥ ገብተን የታገልነው ነፃነት ፍለጋ ነው። ፓርቲያችንም ለሁሉም ዜጎች እኩልነት፣ መከባበር፣ እንደልባችን እንድንናገር እና በሰላም ወጥተን በሰላም ለመግባት እንድንችል ነው የተደራጀነው። እንኳን በፓርቲያችን ውስጥ ገዢውን ፓርቲ እየጠየቅን እየታገልን ያለው እኩልነት ለማስፈን ነው። ይህን አመለካከት ይዤ ነው ወደጉባኤው የገባሁት፣ በጉባኤው ያየሁት ግን እጅግ አሳዛኝ ተግባር ነበር። እሱም፤ ኢንጅር ኃይሉ ሻውል የባላይ ጠባቂ መሆናቸውን ነው ከዚህ በፊት የምናውቀው። ስብሳበው ሲጀመር እሳቸው የፖርቲው መሪ ሆነው ተመለከትናቸው። ለጊዜው ምንም ማለት አልቻልንም።*

*ስብሳበው ሲጀመር የህዝብ መብት ወደጎን ተትቶ የቡድን ስራ ሆነ። ከብዙ ቦታዎች የመጣነው አባለት ብዙ የህዝብ ጥያቄዎችን ይዘን ነበር። ስለሕዝቡ የተነሳ ነገር የለም። መድረኩን የሚመሩት የሚያዙት ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል ብቻ ሆኑ። በጉባኤው መካከል መድረኩን የሚመራ ከጉባኤው ውስጥ የተወጣጣ ይመረጥ። ብዙ የህዝብ ጥያቄዎች አሉ አለን። ምርጫው ከመከናወኑ በፊት ብዙ ውይይት የሚፈልጉ ነገሮች አሉ የሚሉ ጥያቄዎችን አነሳን፣ የሚሰማን አጣን። ጥያቄያችን ተቀባይነት አጣ። ይህን ሁሉ ያደረጉት*

ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል ናቸው። የሚገርመው የበላይ ጠባቂ ታዛቢ እንጂ የጉባኤም አባል አይደለም። እሳቸው ፍላጎታቸውን ጭነው ስብሰባው ተጠናቀቀ፣ ይዘን የመጣነው የሕዝብ ጥያቄዎች ሳይቀርቡ፣ ምላሽም ሳያገኙ ተበተንን። በተፈጠረው ሁሉ አዝናለሁ።”

**አቶ ደምስ ከሰሜን ሸዋ ባሰና ወራና የወረዳው አደራጅ** “ጉባኤው ላይ ልካፈል የመጠሁት ከአካባቢ የሚነሱትን ጥያቄዎች ለማቅረብ ነው። ስብሰባው ሲጀመር ግን የሁሉንም ጥያቄዎች መቀበል ስለማንችል የተወሰኑትን ብቻ ለመመለስ እንሞክራለን አሉ። ጥያቄ ለመጠየቅ እጅ ስናወጣ ግን እሳቸው አደራጅተው ላስገቡት ቡድኖች ብቻ እድል ይሰጡ ጀመር። ተደጋጋሚ ሙከራ ብናደርግም እድል ነፈጉን። የህዝብ ቅሬታን የማያዳምጥ እና የማይመልስ ጉባኤ እንዴት ጉባኤ ሊሆን ይችላል። እሳቸው የመጡት ላደራጁት ቡድን ስልጣን ለመስጠት ነው።

እሳቸው እርቅ ብሎ የሚናገር ቡድን አደራጅተው የመጠይቅ መብት ለእነሱ ብቻ ሲሰጡ ነበር። እርቁን የተቃወመ ጉባኤተኛ የለም። ጉባኤው ያለው እነማሙሸት አማረ ይመለሱ ግን ለአንድ አመት በተራ አባልነት ይቀጥሉ ነው። ይህን የጉባኤውን ሃሳብ ማን ያዳምጥ። ረብሻው ፉጨቱ ማንችሎት። በጓሮ በር ጨርሰውት የመጡትን ስልጣን ፓርቲው ላገዳቸው ግለሰቦች አከፋፈሉት። ፈጽሞ ከእሳቸው የማይጠበቅ ተግባር አከናወኑ። ከፓርተው በላይ ሆነው ፉላጎታቸውን ፈጸሙብን። ትላንት በ800ሺ ብር ምዝበራ ክስ እሳቸው ራሳቸው መስርተው ዛሬ የወንጀሉ ጉዳዩ ሳይጣራ ለጠቅላላው ጉባኤ ሳይቀርብ ሁሉም ነገር በሸፍንፍን አለፈ። ኢንጅነሩ ለምን ፓርቲውን ማተራመስ እንደፈለጉ ግን አልገባንም። እርቅ ከእውነት የሚፈልጉ ከሆነ በምርጫ ዘጠና ሰባት ከእሳቸው ጋር በነበራቸው ልዩነት ፓርቲውን የሸሹትን ጠርተው እርቅ ማውረድ ነበረባቸው። ይህን ማድረግ ግን አልፈለጉም። ያደረጉት ጠቅላላ ጉባኤው ውስጥ የተሰገሱ የጠቅላላው ጉባኤ አባላት ያልሆኑ ድምፆችን በመጠቀም ትላንት በወንጀል ሲከሱት የነበረውን ማሙሸት አማረን የፓርቲው ፕሬዝደንት አድርገው ሰየሙት። ያሳዝናል። ፖለቲካ እንዲህ ከሆነ ፓርቲያችን አምነን እስካሁን የከፈልነው ዋጋ አፈር በላ ማለት ነው። ለኢንጅነሩ መጠቀሚያ መሆናችን ግን አሳዛኝ ነው”

**አቶ ስለሺ ዳበሳ ምዕራብ ሸዋ አመያ ወረዳ የወሊሶ ዞን ተጠሪ** “የዛሬ አራት ዓመት ከፓርተዊ የተገለሉት እነማሙሸት አማረ ፓርቲውን እንዲመሩ ኢንጅነሩ ውሳኔ

*አስተላልፈዋል። እኔ ከአካባቢዬ አባላት በብዛት መዝግቤ ለፓርቲው ሳመጣ ያለኝን ማሙሽት ያውቀዋል። በሱ ጠባብ አመለካከት መኢአድ ሲመራ ማየቱ በጣም ያስቆጣል። ኢንጅነሩም ለብዙ ነገሮች የሚበቁ መስለውኝ ነበር። ከጠባብ አመለካከት ጋር ሳገኛቸው ግን አዝኛለሁ።*

***መሐመድ ጋዳፌ የላፍቶ ክፍለ ከተማ የፓርቲው ፀሐፊ*** *"የጠቅላላ ጉባኤ አባል ነኝ። ጉባኤው ስብሰባ ሲጀመር ኢንጅነር ሃይሉ መሐመድ ከነባለቤቱ ከዚህ ጉባኤ ካልወጣ ስብሰባው አይካሄድም አሉ። ጉባኤውንም ረበሹት። ከስብሰባም እንድወጣ ተደረገ። የሚያሳዝነኝ እሳቸው የጉባኤው አባል ሳይሆኑ፣ ቲፎዞ ይዘው ወደ ጉባኤው በመግባት እኔን የጠቅላላ ጉባኤ አባል ከሕግ ውጪ ከስብሰባው እንድወጣ ተደረገ። ተምሯል ተብሎ ከሚጠበቅ አንድ ትልቅ ሰው ይህን ነውር ማየት አሳፋሪም፣ አሳዛኝም ነበር።*

*ኃይሉ ሻውል ከእምነቴና እሳቸው ላይ ካለኝ አመለካከቴ ጀምሮ ከበፊትም ጫናቸው ይበረታብኛል። በዚህ ጉባኤ ላይ ግን መሰብሰብ የእኔ መብት እንጂ የሳቸው አልነበረም። የበላይ ጠባቂ ታዛቢ እንጂ የፓርቲ ጉባኤ አይመራም። ምን አልባትም ሃይሉ ሻውል የመጀመሪያው ሰው ሳይሆኑ አይቀርም። ከፓርቲው በሕግ አግባብ የተባረሩ ቡድኖችን ሰብስበው በውጭ ታርቀው ጉባኤውን ንቀው አምጥተው በፓርቲው ላይ አስቀመጧቸው። እኛም ይህን አሳዛኝ ታሪክ ተመለከትን። ለእሳቸው በጣም አዝናለሁ። አሳፋሪ ስራ መፈጸማቸውን ሊገነዘቡት ግን ይገባል"*

ኢ/ር ሃይሉ ሻውል በጠሩት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ድነገት የሊቀመንበር ስልጣናቸው ተገፎ ከመድረክ ተጎትተው እንዲወርዱ ተደርጎ በምትካቸው እርሳቸው የማያውቋቸውና ያልጠሯቸው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተገኙበት አቶ ማሙሸተ አማረ ሊቀመነበር ሆነው መመረጣቸውን አቶ አበባው መሃሪ አልተቀበሉትም። የአመራር ሹም ሽሩ "ህገወጥ ነው" ባይ ናቸው። ሁኔታውን "መፈንቅለ ስልጣን" ሲሉ ጠርተውት እንደነበረም ይታወሳል። ከላይ እንደተመለከትነው ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መሃከልም ያልተቀበሉት በርካቶች ናቸው።

ይህ ሁኔታ መኢአድን በአመራር ጉዳይ  አለመግባባት ላይ መሆኑን በግልፅ ያሳያል። ሁኔታው በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመራር እንዳይኖር አድርጓል። ይህን

የአመራር ውዝግብ ሳያጠራ ፓርቲው ወደምርጫ መግባቱ ከፓርቲ ውክልና እንዲሁም እጩዎች ውክልና ጋር የተያያዘ ውዝግብ መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ከምርጫም በኋላ ቢሆን የትኛው ወገን ነው የህዝብ ውክልና ያለው የሚለው ጉዳይ ማወዛገቡ አይቀሬ ነው። በመሆኑም ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ተአማኒ ምርጫ እንዲካሄድ የማድረግ ሃላፊነት የተጣለበት ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፓርቲው ወደ ምርጫ ከመግባቱ በፊት የአመራር ውዝግቡን እንዲያጠራ መጠየቁ ተገቢ ነው። መኢአድ ምርጫ ቦርድ ባቀረበው ጥያቄ ላይ እስካሁን ያለው ነገረ የለም።